# የልጄ በሽታ ትምህርት ቤት ከመሄድ የሚከለክል ነው ወይ?



## ትምህርት ቤት ይላክዋቸው፦

- የአፍንጫ ፍሳሽ ወይም አልፎ አልፎ ማሳል፣ ሌሎች ምልክቶች ከሌሉባቸው
- ትኩሳት ከሌለባቸው እና ባለፉት 24 ሰዓታት ውስጥ ትኩሳትን ለማከም ምንም አይነት መድሃኒት ካልወሰዱ
- ቀላል ያለ የሆድ ህመም
- ከጥቂት የአይን ፍሳሽ ጋር የአይን መቅላት ወይም አይን መቅላት ብቻ፣ ሌሎች ተጨማሪ ምልክቶች ከሌሉባቸው

STAY HOME

## እቤት ያቆይዋቸው፦

- 100.4°F (38°C) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ትኩሳት
- ባለፉት 48 ሰዓታት ውስጥ ማስታወክ እና/ወይም ተቅማጥ
- የማያቋርጥ ሳል **እና** በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ አለመቻል

## የሕክምና እርዳታን ይሹ፦

- ከሚከተሉት ምልክቶች ውስጥ አንዳቸውን ጨምሮ ከ100.4° F (38°C) ከዚያ በላይ የሆነ ትኩሳት፦ የጆሮ ህመም፣ የጉሮሮ ህመም፣ ሽፍታ፣ የሆድ ህመም፣ የራስ ምታት ወይም የጥርስ ህመም
- ከባድ የሆድ ህመም ወይም ተማሪው ትኩሳት፣ ደም የተቀላቀለበት ወይም ጥቁር ሰገራ ወይም የሰውነት ውሃ እጥረት ካሉባቸው (ድካም እና እንቅልፍ እንቅልፍ ማለት፣ የአፍ መድረቅ) እና/ወይም ባለፉት 8 ሰዓታት ውስጥ ሽንታቸውን ካልሸኑ
- ከባድ ሳል ወይም ተማሪው ትኩሳት ወይም የመተንፈስ ችግር ወይም አስም ካለባቸው
- ትኩሳት፣ ወፍራም ፈሳሽ፣ እብጠት፣ የአይን ህመም ወይም የአይን ጉዳት ያካተተ የአይን መቅላት
- ፈሳሽ የያዙ፣ የሚያሰቃዩ፣ ጠባሳ የሚመስሉ ሽፍታዎች፣ ቁስሎች እና/ወይም ትኩሳት ካሉባቸው
- ከባድ ህመም ወይም ጉዳት
- ስጋት ካለብዎት እና/ወይም ልጅዎ ቀጣይ የሆነ የጤና ስጋት ካሉባቸው
- ለትምህርት ቤቱ የሚሰጥ የዶክተር ማስታወሻ እንዲሰጥዎት ይጠይቁ።

**ልጅዎ ከትምህርት ቤት የሚቀሩ ከሆነ ት/ቤቱን ያሳውቁ!**

Amharic

## የትምህርት ቤት የጤና መመሪያ

ልጆች በአጠቃላይ ጤናማ ከሆኑ እና በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ የሚችሉ ከሆነ ወደ ትምህርት ቤት ይላኩ!

ልጅዎን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ወይም አለመላክ እንዳለብዎት የማያውቁ ከሆነ ወይም ስለ ልጅዎ ጤና የተለየ ስጋት ካለዎት የትምህርት ቤትዎን ነርስ ወይም የልጅዎን የህክምና አገልግሎት ሰጪ ያነጋግሩ!

Arlington Public Schools

ለበለጠ መረጃ፡
www.apsva.us/health-safety/illness